ኖቬምበር 13 ቀን 2023 በሚጀምረው ሳምንት ላይ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ክትትል ቢሮ የኬምብሪጅ ኮሚዩኒት ቻርተርድ ትምህርት ቤት ላይ ክትትልና ግምገማ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ክትትል ቢሮ በየሦስት ዓመቱ እያንዳንዱን አውራጃና የቻርተር ትምህርት ቤት በመጎብኘት የፌዴራልና የግዛቶችን የልዩ ትምህርትና የሲቪል መብቶች ደንቦች አክብረው መሥራታቸውን ይመዝናል፡፡ ከልዩ ትምህርት ጋር የሚያያዙ የግምገማ አቅጣጫዎች የተማሪዎች ምዘናን፣ የቅበላ አወሳሰንን፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚዘጋጅ የትምህርት ፕሮግራምን (ኢንዲቪጁዋላይዝድ ኤጁኬሽን ፕሮግራም - አይ ኢ ፒ) የቡድን ሒደት፣ ቀረጻና ትግበራን ያካትታሉ፡፡ ከሲቪል መብቶች ጋር የሚገናኙ የግምገማ አቅጣጫዎች ደግሞ የተማሪዎች ሌላ ተማሪን ማስፈራራትንና ማሸማቀቅን፣ የተማሪ ዲሲፕሊንን፣ አካላዊ ገደብንና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ለሁሉም ተማሪዎች በእኩል ተደራሽ መሆንን ያካትታሉ፡፡

የክትትል ቢሮው በአካል በትምህርት ቤቱ ከሚያደርገው ጉብኝት በተጨማሪ ወላጆችንም የሚያነጋግር ሲሆን ይህም የግምገማው ሒደት ቁልፍ አካል ነው፡፡ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የክትትል ቢሮ የግምገማ ሰብሳቢ የአካል ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች ወላጆች በሙሉ በልጃቸው የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ዋና ዋና አቅጣጫዎች ላይ የሚያተኩር የኦንላይን ዳሰሳ ይልካሉ፡፡ የዳሰሳው ውጤት በኋላ ለሚዘጋጀው ሪፖርት ግብዓት ይሆናል፡፡ በትምህርት ቤት ጉብኝት በሚያደርግበት ወቅት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ክትትል ቢሮ ለአንድ የአውራጃው የልዩ ትምህርት አማካሪ የወላጅ ጉባዔ አባል ቃለ መጠይቅ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ለአውራጃው ሠራተኞችና አመራሮች ቃለ መጠይቆች፣ የተማሪ ሪከርዶች ቅኝትና የትምህርት ቤት ምልከታ የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የስልክ ቃለ መጠይቅ ለማስያዝ የሚፈልጉ ተማሪዎችና ሌሎች ግለሰቦች የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ክትትል ሰብሳቢ የሆኑትን ጂል ላንጅን በ gillian.e.lange@mass.gov ላይ ሊያገኟቸው ይችላሉ፡፡ በቃለ መጠይቅ ለመሳተፍ የትርጉምና ሌሎች አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ሰው ካለ መምሪያው አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል፡፡

ቢሮው በአካል ተገኝቶ ትምህርት ቤቱን ከጎበኘ ከ60 ቀናት ገደማ በኋላ የክትትል ሰብሳቢዋ አውራጃው በደንቦቹ ላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች/ተፈላጊዎች የሚያሟላባቸውን ወይም በላቀ ደረጃ የሚያሟላባቸውን አቅጣጫዎች እንዲሁም መስተካከል ወይም መሻሻል በሚገባቸው አሠራሮች ላይ አውራጃቸው እገዛ የሚፈልግባቸውን አቅጣጫዎች የያዘ ሪፖርት ለአውራጃው እንዲደርስ የሚያደርጉ ይሆናል፡፡ ሪፖርቱን ላይ ማግኘት የሚችሉ ይሆናል http://www.doe.mass.edu/psm/tfm/reports/.